# ምናለበት?!

(ለአምባገነኖችና ለግብረ-አበሮቻቸው)

የሕዝብ ራዕይ ባታመክኑ፣
ያገር ተስፋ ባታተኑ፣
ያያችሁትን ፍጡር ሁሳ - እንደ ዕብድ ውሻ ባትለክፉ፣
የትውልድን ውብ አበባ - በጭካኔ ባትቀጥፉ፣
ያድባር ቆሌ ባትገፉ፣ የጡር እንባ ባታተርፉ፣
ጣፋጭ ሲሳይ ማር ወለላ - በሬት መራር ባትለውሱ፣
ምናለበት?! ቀኑ እክትሞ - ከመንበሩ ብትነሱ!

በሥልጣን ጥም ባትሰክሩ፣
ካይጥ ጉድገጓድ - የቆቅ ኑሮ ባትኖሩ፣
መውጫ መግቢያው ባይጠባችሁ - ጥላችሁን ባትፈሩ፣
እኩይ ድርጊት ተደራርቦ - ሰው ፊት መቅረብ ባታፍሩ፣
አራጅ፣ ውራጅ... አምባገነን - የሰቆቃ የጭካኔ...፣
የዲያቢሎስ ቁራጭ ቁንጮ - ሠይጣን፣ አውሬ፣ አረመኔ...
ተብላችሁ ተንቃችሁ - የውርደት ሥም ባትለብሱ፣
ምናለበት! ለክብራችሁ፣- ላገር ክብር ብትሳሱ!

ልጆቻችሁ ያልታደሉት፣
ፍርሃት ታቅፈው የሚኖሩት፣
አንገት መድፋት፣ መሸማቀቅ፣ - ሽብር፣.. ሥጋት ሳይገባቸው፣
ባደባባይ ቢራመዱ - ልበ-ሙሉ ኩሩ ሆነው...፧

ሕዝብ ሲራብ፣ አገር ሲወድም - ጥሪት ማሸሽ በያለበት፣
ላትበሉት ለዝንተ-ዓለም - ላትኖሩ ምዕተ-ዓመት፣
መኖር ከቶ እንዲያኮራ - በንጽህና በነጻነት፣
ከማንዴላ...፣ ከኦባማ.. - ብትማሩ ምናለበት?!

የብዙኃን ምክር፣ ቁጣ.. - የሕዝብ ድምጽ ባትንቁ፣
ልቦናውን ቢሰጣችሁ - ከእንቅልፋችሁ ብትነቁ፧
ብልጽግና፣ ሰላም፣ ፍቅር፣ - ፍትህ፣ ጤና.. እንዲያብቡ፣
ሰብዓዊነት እንዲሰፍን - እፎይ ብሎ ሊኖር ሕዝቡ፣
እንዲከበር ክቡር ድምጹ - ሳያሰልስ ሲወተውት፣
ሳትተብቱ ብትሰሙ - ቢያምርባችሁ ምናለበት?!

አልያ ግን ካልገባችሁ - የሕዝብ እንባ ያገር ብሶት፣
አሁን ደርሶ ምናለበት?! - ቢጠርጋችሁ አንድ መዐት!!

ጌታቸው አበራ
ኅዳር ፳፻፩ ዓ/ም
(ኖቬምበር 2008)